TRUST Contraceptive Implants

# *Trust-Implant (II)®*

*(levonorgestrel subdermal contraceptive implant)*



- *Low cost,*
- *Safe, and*
- *Effective Contraceptive implant*
- *Now available with a disposable Trocar*

dkt Social Marketing for a better Life

TRUST Contraceptive Implants

# ትረስትኢምፕላንት(2)

በክንድ የሚቀበሩ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎች ዋጋው በግማሽ ያነሱ ነው፡፡



- በዝቅተኛ ዋጋ
- አስተማማኝ
- ውጤታማ የወሊድ መከላከያ
- አሁን በቀላሉ የሚገኝ ሲሆን ለአንድ ጊዜ አገልግሎት ብቻ ከሚውለው የማስገቢያው መርፌ ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው፡፡

dkt Social Marketing for a better Life

# *Trust-Implant (II)®*

## Subdermal contraceptive implant

*Trust-Implant* is ~~a~~ subdermal contraceptive implant manufactured in China by Shanghai Dahuna Pharmaceutical Co.,Ltd. The implant is composed of two thin, flexible rods made of medicalgrade silicon, each containing 75mg levonorgestrel (a synthetic progestin). Each rod consists of the drug core and an external medical silastic tube sealed at both ends with medical adhesive. The implant is inserted under the skin in the upper arm.

*Trust-Implant has the same mechanism of action as Jadelle. Like other contraceptive implants, Trust-implant is one of the most highly effective contraceptive methods, and has an annual pregnancy rate below 1%. The implants are currently labeled for four years of use*

*Trust-Implant (II)®*

- Provide highly effective, long-acting, and 4 years of pregnancy protection
- Each *Trust-Implant (II)® has a disposable trocar for Insertion*
- Two rod system with 75 mg of levonorgestrel in each rod
- Made of medical grade silastic
- Dimensions: 2.4 mm x 44 mm
- Manufactured by Shanghai Dahua Pharmaceuticals co, Ltd
- Although insertion and removal require a trained provider, both procedures are done quickly
- Contraceptive protection is immediately reversible upon implant removal; implants have no impact on long-term fertility

## ትረስት ኢምፕላንት (II)®

(ሊቮኖጀስትሪል) ከቆዳ ስር የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያ
ዝቅተኛ ዋጋ አስተማማኝ እና ውጤታማ በቆዳ ስር የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያ

## በቆዳ ስር የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያ

ትረስት ኢምፕላንት ሻንግሀይ ዳሁና ፋርማሲውትካል ማኅበር በሚባል የቻይና ኩባንያ የሚመረት ሲሆን ከ ሲልከን የተሰሩ ሁለት ቀጭንና ተጣጣፊ ዘንጎች የያዘ ነው፡፡ ሁለቱም ዘንጎች እያንዳንዳቸው 75 ሚ.ግ ለቮኖገስትሪል ይይዛሉ፡፡ ዘንጎቹ መድሀኒቱን በውስጣቸው የያዙና ከላይ በ ሲላስቲክ ትቦ የተሸፈኑ ሲሆን ትቦው በሁለቱም ጫፍ በኩል በማጣበቂያ የተጣበቀ ነው፡፡ ትረስት ኢምፕላንት በክንድ ላይ በቆዳ ስር የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያ ነው፡፡

ትረስት ኢምፕላንት ወሊድን የመቆጣጠሪያ መንገዱ ልክ እንደ ጃዴል አይነት ሲሆን እንደሌሎቹ በቆዳ ስር የሚቀበሩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ትረስት ኢምፕላንት እጅግ ውጤታማ ነው፡፡ ከሚጠቀሙት ሴቶች በአመት 1% በታች በሚሆኑት ላይ ብቻ እርግዝና ይከሰታል፡፡ ትረስት ኢምፕላንት ለ4 አመት እርግዝና ይከላከላል፡፡

## ትረስት ኢምፕላንት (II)®

- እጅግ አስተማማኝ፣ ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል እና ለ4 ዓመት እርግዝናን ይከላከላል፡፡
- እያንዳንዱ ትረስት ኢምፕላንት ለአንድ ጊዜ የሚሆን ከቆዳ ስር ማስገቢያ መሳሪያ አለው፡፡
- እያንዳንዳቸው 75 ሚ.ግ ለቮኖርገስትሪል የያዙ 2 ዘንጎች አሉት፡፡
- ለህክምና የሚያገለግል ጥራት ባለው ሲላስቲክ የተሰራ
- መጠኑ 2.5 ሚ.ሜ x 44 ሚ.ሜ
- በሻንግሀይ ዳሁና ፋርማሱቲካል ማህበር የተሰራ
- ምንም እንኳን በቆዳ ስር ለመቅበርና ለማስወገድ የህክምና ባለሙያ ቢያስፈልግም ሁለቱም ጉዳዮች ጊዜ የማይወስዱ ስራዎች ናቸው፡፡
- ተቀባሪው የወሊድ መከላከያ ከቆዳ ስር በተወገደ ጊዜ ወዲያውኑ እርግዝና የመከላከል አቅሙን ያጣል፡፡ ተቀባሪው የወሊድ መከላከያ በዘላቂ የመውለድ ችሎታ ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ የለውም፡፡

## መንደርደሪያ

ትረስት ኢምፕላንት ፕሮጀስቲን የያዘ የክብሪት እንጨት መጠን ያለው በክንድ ቆዳ ስር ተቀብሮ ለ4 ዓመታት ፕሮጀስቲንን ቀስ በቀስ የሚለቅ የወሊድ መቆጣጠሪያ ነው፡፡ ወሊድን የመቆጣጠሪያ መንገዱ በሴት የመራቢያ አካል ውስጥ የሚገኘውን ፈሳሽ በማወፈር (የወንድ የዘር ፍሬን እንደልቡ ተንቀሳቅሶ የሴቲቷ የዘር ፍሬ ጋር እንዳይደርስ በማድረግ) እና የሴት የዘር ፍሬ እንዳይለቀቅ በማድረግ ነው፡፡ ዲኬቲ ኢትዮጵያ ይህንን ሁለት ዘንግ ያለው ትረስት ኢምፕላንት የወሊድ መቆጣጠሪያ አቅርቧል፡፡

## Background

*Trust-Implant (II)®* is matchstick-sized rods that contain progestin. Implanted beneath the skin of a woman's upper arm, the progestin is slowly released for 4 years. *Trust-Implant (II)®* interrupt fertility by thickening cervical mucus (mechanically preventing the sperm from accessing the ovum) and through hormonal effects that prevent ovulation in about half of menstrual cycles. DKT Ethiopia is introducing the new two-rod implant systems *Trust-Implant (II)®*.

***Implant types:*** The most common contraceptive implants include:

- *Jadelle:* 2 rods, provides contraception for 5 years
- *Implanon:* 1 rod, provides contraception for 3 years
- *Trust-Implant (II):* 2 rods, provides contraception for 4 years

***Method characteristics:*** *Trust-Implant (II)®* are highly effective at preventing pregnancy, long-acting, totally user-independent, and completely and immediately reversible upon removal. Unlike some other hormonal forms of contraception, implants can be used by cigarette smokers, women who have risk factors for cardiovascular disease (including high blood pressure), and women who are breastfeeding (after 6 weeks postpartum).

Insertion requires a minor surgical procedure by a trained practitioner using appropriate aseptic technique in a sterile surgical environment. As with other hormonal contraceptive methods, some women experience side effects such as headaches, breast tenderness, mood changes, nausea, and unpredictable vaginal bleeding—all of which usually decrease over time. Unpredictable vaginal bleeding associated with the use of implants sometimes leads users to have the implants removed, so appropriate counseling is essential to reduce discontinuation. *Trust-Implant (II)®* is inserted in the same way as *Jadelle*.

***Health benefits:*** Unlike some other hormonal forms of contraception, *Trust-Implant (II)®* do not contain estrogen, so women can safely breastfeed with an implant in place. Because implants may cause menstrual bleeding to be lighter, less frequent, or absent, some users may have a decreased risk of iron-deficiency anemia. Users also gain protection against health risks associated with pregnancy, pelvic inflammatory disease, and ectopic pregnancy. Implants have no effect on sexual function.

## በቆዳ ስር የሚቀበሩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች

- ጃዴል - ሁለት ዘንጐች፡ ለአምስት አመት እርግዝናን ይከላከላሉ፡፡
- ኢምፕላኖን - አንድ ዘንግ፡ እርግዝናን ለ3 አመት ይከላከላል፡፡
- ትረስት ኢምፕላንት - 2 ዘንጐች፡ እርግዝናን ለ4 አመት ይከላከላል፡፡

## የትረስት ኢምፕላንት ባህሪዎች

ትረስት ኢምፕላንት እጅግ ውጤታማ፡ ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል፡ በተጠቃሚው አይነት ያልተወሰነና ከቆዳ ስር ከተወገደ በኋላ ወዲያው የመከላከል አቅሙን የሚያጣ በቆዳ ስር የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያ ነው፡፡ ትረስት ኢምፕላንት ከሌሎች የወሊድ መቆጣጠሪያዎች የሚለየው

- በሲጋራ አጫሽ ሴቶች ጥቅም ላይ መዋል መቻሉ
- ለልብና ለደም ቧንቧ በሽታዎች (ደም ግፊትን ጨምሮ) የመያዝ እድላቸው ሰፊ በሆኑ ሴቶች ጥቅም ላይ መዋል መቻሉ
- በሚያጠቡ ሴቶች (ስድስት ሳምንት ከወሊድ በኋላ) ጥቅም ላይ መዋል መቻሉ

ትረስት ኢምፕላንት በቆዳ ስር ለማስገባት ቀላል ቀዶ ጥገና የሚያስፈልግ ሲሆን ቀዶ ጥገና በባለሙያ መካሄድ አለበት፡፡ ይህ የሚከናወንበት ቦታ ንጹህና ከበሽታ አምጪ ተዋህስያን የጸዳ መሆን አለበት፡፡ እንደሌሎቹ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ሁሉ ትረስት ኢምፕላንት በአንዳንድ ሴቶች ላይ እራስ ምታት፡ የጡት መጠጠር፡ የባህሪ ለውጥ፡ ማቅለሽለሽ እና ያልተጠበቀ ደም በብልት መፍሰስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ እነዚህ የጐንዮሽ ጉዳቶች በጊዜ በኋላ እየቀነሱ የሚመጡ ይሆናል፡፡ ያልተጠበቀ ደም በብልት መፍሰስ በሚያጋጥምበት ጊዜ አንዳንድ ተጠቃሚዎች የወሊድ መቆጣጣሪያውን እንዲቋረጥ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ አይነት ሴቶችን አግባብ ያለው ምክር በመስጠት የወሊድ መቆጣጠሪያው እንዳይቋረጥ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ትረስት ኢምፕላንት በቆዳ ስር የሚቀበረው ልክ እንደ ጃዴል ነው፡፡

## ትረስት ኢምፕላንት የሚሰጣቸው የጤና ጥቅሞች

ትረስት ኢምፕላንት እንደሌሎቹ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ኢስትሮጅንን በውስጡ አልያዘም፡፡ ስለዚህ የሚያጠቡ ሴቶች ሊጠቀሙት ይችላሉ፡፡ ትረስት ኢምፕላንት የወር አበባ ቶሎ ቶሎ እንዳይመጣ ወይም ጨርሶ እንዲቀር ስለሚያደርግ አንዳንድ ተጠቃሚዎች ከአይረን እጥረት ለሚመጣ የደም ማነስ የመጋለጥ እድላቸው የጠበበ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከእርግዝና ጋር ተያይዞ የሚመጡ የጤና ችግሮችን እና ከማህፀን ውጭ የሚያጋጥም እርግዝና ትረስት ኢምፕላንት ይከላከላል፡፡ ትረስት ኢምፕላንት የግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አያመጣም፡፡

***Conditions that may make use of*** *Trust-Implant (II)®* ***Unsafe:*** In most cases, women with the following conditions should be advised to use a different form of contraception:

- Serious liver disease, such as liver tumor, severe cirrhosis, or active hepatitis
- Current deep venous thrombosis or pulmonary embolus
- Unexplained or unusual vaginal bleeding that requires evaluation
- Current use of antiseizure drugs (barbiturates, carbamazepine, oxcarbazepine, phenytoin, primidone, topiramate) or rifampicin
- Breast cancer (currently or in the past)

In most cases, breastfeeding women who are fewer than six weeks post-partum should delay initiation of contraceptive implant use.

***Sexually transmitted infections and HIV/AIDS:*** *Trust-Implant (II)®* provide no protection against STIs and HIV/AIDS. A male or female condom should be used to decrease the risk of transmission. Women with HIV/AIDS can use *Trust-Implant (II)®*, but should also use a barrier method to decrease the risk of disease transmission.

## Programmatic Considerations

Offering Trust-Implant (II)® as a contraceptive choice requires that trained practitioners perform the minor procedures necessary to either insert or remove the device in a reliably aseptic environment. Counseling should also be made available to potential recipients, so that they clearly understand implant insertion and removal procedures, the risks and benefits of implant use, as well as what to expect in terms of side effects, particularly bleeding changes.

Trust-Implant (II)® is cost effective when used long term. The procurement price is less than ½ of other implant

### Disposable Trocar

A disposable trocar for Trust-Implant (II)® Insertions is available. The disposable trocar eliminates the need to clean the trocar by autoclaving after each use and facilitates service delivery in decentralized settings where access to electricity cannot always be ensured.

## ትረስት ኢምፕላንትን ከመጠቀም የሚከላከሉ ሁኔታዎች

እነዚህ ሁኔታዎች ያጋጠሟቸው ሴቶች ሌላ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንዲጠቀሙ ይመከራሉ።

- የጉበት እጢ፣ የጠና ሲሮሲስ፣ የጉበት በሽታን የመሳሰሉት አደገኛ የጉበት ህመሞች
- የደም መርጋት
- መመርመር ያለበት ምንነቱ ያልታወቀ ወይም ያልተለመደ ከብልት የሚፈስ ደም
- በቅርብ ጊዜ የሚከተሉትን መድሀኒቶች መድሀኒት የተጠቀሙ ከሆነ (ባርቢቹሬትስ፣ ካርማዘፒን፣ እክስካርማዘፒን፣ ፌኒቶይን፣ ፕሪሚዶን፣ ቶፒራሜት) ወይም ሪፍምፒሲን
- የጡት ካንሰር (አሁን ወይንም ከዚህ በፊት ያለባቸው)

ከወለዱ ከ6 ሳምንት በታች የሆናቸውና ጡት እያጠቡ ያሉ ሴቶች ትረስት ኢምፕላንት ለመጠቀም ጊዜው እስኪደርስ መታገስ አለባቸው።

## የአባላዘር በሽታዎችና ኤች አይ ቪ ኤድስ

ትረስት ኢምፕላንት የአባላዘር በሽታዎችንና ኤች አይ ቪ ኤድስን አይከላከልም። ስለዚህ እነዚህ በሽታዎችን ለመከላከል የወንድ ወይንም የሴት ኮንዶሞችን መጠቀም ያስፈልጋል። ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለባቸው ሴቶች ትረስት ኢምፕላንትን መጠቀም ይችላሉ። ነገር ግን ከትረስት ኢምፕላንት በተጨማሪ በሽታው እንዳይተላለፍ ኮንዶሞችን መጠቀም ያስፈልጋል።

## ፕሮግራሙን ለመጀመር መታሰብ ያለባቸው ነገሮች

ትረስት ኢምፕላንት ለተጠቃሚ በሚሰጥበት ወቅት ከቆዳ ስር ለማስገባትንና ለማውጣት ባለሙያና ንጹህ የሆነ የቀላል ቀዶ ጥገና ቦታ ያስፈልጋል። ትረሰት ኢምፕላንትን ሊጠቀሙ ለሚችሉ ሴቶች ምክር መስጠት ያስፈልጋል። ይህ ምክር የትረስት ኢምፕላንትን ያጠቃቀም ሁኔታ (ማለትም ከቆዳ ስር ማስገባትና ማውጣት)፣ ጥቅምና ጉዳቱን እንዲሁም የጐንዮሽ ጉዳቶችን (በተለይ የወር አበባ ኡደት ላይ ለውጦችን) በደንብ እንዲረዱት ያደርጋል።

እንደ ዋጋ አወጣጡ ሆኖ ትረስት ኢምፕላንት ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል ወጪ ቆጣቢ የወሊድ መቆጣጠሪያ ነው። ይህ የመከላከያ ዘዴ ከሌሎች በክንድ ከሚቀበሩ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎች ዋጋው በግማሽ ያነሰ ነው።

## ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ከቆዳ ስር ማስገቢያ መሣሪያ

ትረስት ኢምፕላንት ካስገባን በኋላ የሚጣል ከቆዳ ስር የማስገቢያ መሣሪያ አለው። ይህ ከጥቅም በኋላ የሚጣል መሣሪያ አንድ ጊዜ ከተጠቀሙ በኋላ በአውቶክሌቭ የማጽዳት ግዴታን ያስወግዳል። እንዲሁም ባልተማከሉ ቦታዎች ላይ ወይም መብራት እንደልብ የማይገኝባቸው ቦታዎች ላይ የተሻለ አገልግሎት ይሰጣል።